**መቀሌ የሁላችንም ናት !**

ግርማ ካሳ
(muziky68@yahoo.com)



መጋቢት 18 2001

አሁን በስልጣን ላይ ያለዉ የሕወሃት መንግስት ስልጣን ሊጨብጥ እንዲችል ካስቻሉት ምክንያቶች አንዱ በትግራይ የሚገኙ ኢትዮጵያውያን የከፈሉት ትልቅ መስዋእትነት ነዉ። የትግራይ ወጣቶች ሕወሃትን የተቀላቀሉት ኢትዮጵያ ባህር አላባ እንድትሆን፣ በዘርና በኃይማኖት እንድትከፋፈል፣ የኢትዮጵያ ግዛት ለጎሮቤት አገር እንዲሰጥ፣ በደርግ ከነበረዉ ያልተናነሰ አፈናና የሰብዓዊ መብት ረገጣ እንዲኖርና የኢትዮጵያ ንጹህ አረንጓዴ ቢጫ ቀይ ሰንደቅ አላማ መሬት እንዲጣል አልፎም እንዲለባበጥ አልነበረም።

እነዚህ ወጣቶች የታገሉትና የሞቱት በኢትዮጵያ የግፍ ስርዓት ተወግዶ፣ በሕዝብ ላይ የተጫነዉ ቀንበር ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ እንዲነሳ ነበር። አስታወሳለሁ፣ ሕወሃት በአዲስ አበባ ያለዉን የሬዲዮ ጣቢያ ሲቆጣጠር አንድ የሕወሃት ተጋዳይ የተናገሩትን። “የሕዝብ ብሶት የወለደዉ ጀግናዉ የኢሕአዴግ ሰራዊት ሬዲዮ ጣቢያዉን ለሰፊዉ ሕዝብ ጥቅም ተቆጣጥሮታል” ነበር ያሉት። ተጋዳዮቹ የሕዝብ ብሶት እንደወለዳቸዉና የሕዝብን ብሶትን አስወገደዉ፣ የሕዝብን ጥቅም ለማስከበር እንደታገሉ የሚገልጽ ትልቅ አባባል ነበር።

ነገር ግን ብዙዎች ደማቸዉን ያፈሰሱለት ትግል በጥቂቶች ተሰርቆ ( hijacked ሆኖ) አገራችን ኢትዮጵያ አሁን ያለችበት አሳዛኝ ሁኔታ ላይ ትገኛለች።

ለኢትዮጵያ ነጻነት፣ የኢትዮጵያዉያን ደም የፈሰሰባቸዉ እንደ ጉንደት፣ ጉራ ፣ አዱሊስ፣ ከሰላ የሚገኙባት፣ የአገራችን ታሪካዊ ግዛት የሆነችዉ ባህር ምድሪን (ኤርትራ) ኢትዮጵያ እንድታጣ ተደርጎ፣ አገራችን ባህር አልባ ለመሆን በቅታለች። ለምለም የአገራችን መሬት ለሱዳን በነጻ እየተሰጠ ነዉ። አገራችን ኢትዮጵያ በዘር ላይ በተመሰረተ ክልሎች ተከፋፍላለች። እያንዳንዱ ክልል ደግሞ ከፈለገ እንደ ኤርትራ ተገንጥሎ መዉጣት የሚችልበት፣ በማንም አገር የሌለ፣ ሕጋዊ መብት ተሰጥቶታል። ኤርትራ በተባበሩት መንግስታት ተቀባይነት እንድታገኝ በጥድፊያ ፊርማ እንደተፈረመና እዉቅና እንደተሰጠ ሁሉ፣ ነገ እንበል ኦጋዴን ልገንጠል ብትል፣ ፊርማ ከማሳረፍ ወደ ኋላ የማይበልበትና ከልካይ የሌለበት ሁኔታ ዉስጥ ነዉ ያለነዉ። **የኢትዮጵያ አረንጉዋዴ ቢጫ ቀይ ሰንደቅ አላም ማዉለብለብ፣ በአርባ ምንጭ የመኢአድ አባላት በቅርቡ እንደደረሰባቸዉ፣ የሚያሳስር ወንጀል ሆኑዋል። (ጣሊያን ኢትዮጵያን ለአምስት አምት ይገዛ በነበረ ጊዜ እንደነበረዉ ማለት ነዉ)**

ታዲያ «እንዲህ አይነት ታላላቅ ጥፋቶች እየተደረጉ እኛ ኢትዮጵያውያን እንዴት ዝም ልንል ቻልን?» የሚለዉ ጥያቄ በብዙዎች ዉስጥ የሚመላለስ ይመስለኛል። ለዚህ ጥያቄ በዋናነት መልስ ሊሆን ይችላል ብዬ የማስበዉ (በርካቶች በዚህ ሊስማሙ ይችላሉ ብዬ አስባለሁ) በጣም በረቀቀ መልኩ ኢትዮጵያዉያንን ከኢትዮጵያዉያን የመከፋፈል ስትራቴጂ አሁን ባለዉ አገዛዝ በሰፊዉ ስለተዘረጋ ነዉ።

የሚያሳዝነዉ ግን እኛ ኢትዮጵያዉያን ለአሥራ ስምንት አመታት፣ ከአመት ወደ አመት አገዛዙ በሚያዘጋጅልን ወጥመድ ዉስጥ አይናችን እያየ እየደጋገምን መግባታችንና፣ «ተጨቁናቹሃል፣ ይኼ ብሄር ብሄረሰብ እናንተን ሲረግጥ ቆይቷል። ይኼ ብሄረሰብ ሊያጠፋህ ነዉ ....» እየተባልን በመካከላችን ጥላቻ እንዲያድግና እንዲስፋፋ፣ እርስ በርስ እንዳንተማመንና እንድንፈራራ እየተደረግን ዝም ማለታችን ነዉ።

በተለይም ለዚህ መሰሪ የጥላቻ ፖሮፖጋንዳ ሰላባ የሆነዉ በትግራይ የሚገኘዉ ወገናችን ነዉ ብዬ አስባለሁ። ሕወሃት የሚያራምደዉ የጥላቻ ፕሮፖጋንዳ፣ በተለያዩ ጊዚያት እንደታየዉ፣ በትግራይ ሕዝብና በተቀረዉ ኢትዮጵያዊ መካከል የመከፋፈልን ግንብ የሚዘረጋ ነዉ። የትግራይ ሕዝብ ሌላዉን ኢትዮጵያዊ እንዲፈራ፣ ሌላዉ ኢትዮጵያዊ ደግሞ የትግራይን ሕዝብ እንዲጠላ የሚያደርግ ዘመቻ ሆን ተብሎ ነዉ እየተደረገ ያለዉ።

ብዙ የትግራይ ተወላጅ ወገኖቻችን፣ ከሚቀርብላቸዉ ጎጂ የዉሸት ፕሮፖጋንዳ የተነሳ፣ ሕወሃት ከተለወጠ የነርሱም ጥቅም እንደሚጎዳ፣ ሌላዉ ኢትዮጵያዊ በነርሱ ላይ ጥላቻ እንዳለዉና እንደሚነሳባቸዉ፣ ምንም እንኳን በሕወሃት ባይደሰቱም ሌላ አማራጭ እንደሌላቸዉ የሚያስቡ አሉ።

በሌላ በኩል ደግሞ የትግራይን ሕዝብ ከሕወሃት ለይተዉ ማየት ያልቻሉ፣ ለተፈጠረዉ ችግር እራሱ እየተጎዳና እየተበደለ ያለዉን የትግራይን ሕዝብ ተጠያቂ የሚያደርጉ፣ ጥቂት ትግሪኛ ተናጋሪዎች በትግራይ ሕዝብ ስም ሲከብሩና ሲበለጽጉ በማየት በድህነትና በችግር ላይ ያለዉ የትግራይ አብዛኛዉ ነዋሪ ተጠቃሚ እንደሆነ በስህተት የሚያስቡና ሕወሃት ከሚያደርጋቸዉ አሳዝኝ ተግብራት በመነሳት በዉስጣቸዉ ቂምና ጥላቻ እያደረባቸዉ ያሉ ወገኖች አሉ።

እነዚህ ሁለት አይነት ወገኖች አሁን ወደሚያስቡት ሃሳብና አሁን ወደደረሱበት ደረጃ ሊደርሱ የቻሉት ያለ ምክንያት አይደለም። ገዢዉ ፓርቲ የሚያከናዉናቸዉን አንዳንድ በጣም የረቀቁና ሰይጣናዊ ሥራዎችን በጥንቃቄና ካለማስተዋል የተነሳ እንጂ።

ለምሳሌ መቀሌ፣ ቱቢንግን በምትባል የአንድ የጀርመን ከተማ «እህት ከተማ» ለመባል በእጩነት መቅረቧ በተመለከተ የተፈጠረዉን ክስተት እንመልከት። የሕወሃት ካድሬዎች መቀሌ የቱቢንግን ከተማ እህት ከተማ ለመሆን መታጨቷን ለርካሽ የፖለቲካ መጠቀሚያ አደረጉት።

አቶ ያእቆብ አብርሐም የተባሉ የሕወሃት ደጋፊ መቀሌን በመቀሌነቷ ከመሸጥ ይልቅ መቀሌን ከሕወሃት ጋር በማገናኘት ለቱቢንግን ባለስልጣናት ደብዳቤ አስገቡ። መቀሌ ለምን መመረጥ እንዳለባት እኚህ የሕወሃት ደጋፊ ከጠቀሱት ምክንያቶች ዉስጥ ሕወሃት የብሄር ብሄረሰቦችን የራስን እድል በራስ የመወሰን መብት እስከመገንጠል እንደደነገገ፣ በፕሬዘዳንት ጂሚ ካርተርና በአዉሮፓ ማህበር ነጻና ፍትሃዊ ምርጫ ተብሎ ተነገረለት ባሉት ምርጫ 97፣ አሁን ያለዉ መንግስት አሸናፊ እንደሆነና ኢትዮጵያ ዉስጥ ሕገ የበላይ እንደሆነ የሚገልጹ አባባሎች ይገኙበታል። [1]

በመጀመሪያ ደረጃ ምርጫ ዘጠኛ ሰባትን በተመለከተ የካርተር ማእከል ምርጫዉን «አሳዛኝ» ሲለዉ የአዉሮፓ ማህበር ደግሞ «አለም አቀፍ መስፈርትን ያልጠበቀ» ብሎ ምርጫዉ በምንም መልኩ ፍትሃዊ እንዳልነበረ ነዉ የተናገሩት። ያም ሆኖ ደግሞ በአገራዊ ደረጃ የተደረገ ምርጫ ከመቀሌ ከተማ ጋር ምን ሊያገናኘዉ እንደሚችል ግራ የሚያጋባ ነዉ። የመገንጠል መብትስ ከመቀሌ ከተማ ጋር ምን አገናኘዉ ? ፍየል ወዲያ ቅምዝምዝ ወዲህ !

[1] http://aigaforum.com/articles/Open_letter_to_mayor_of_Tubingen.htm

**እኚህ የሕወሃት ደጋፊ፣ በደብዳቢያቸዉ የመቀሌ ከተማ በኢትዮጵያ ታሪክ ዉስጥ ትልቅ ቦታ እንዳላት ሲጽፉ አናይም። የመቀሌ ሕዝብ ለኢትዮጵያ አንድነት ያደረገዉን ተጋድሎ ሲጠቅሱ አያናይም።**

የምናየዉ የሰለቸንንና ያደነቆረንን የገዢዉን ፓርቲ ፕሮፖጋንዳን፣ በመቀሌ ስም ሲረጩ ነዉ። በግፍ፣ ሕገ መንግስቱ ተጥሶ በጉልበተኞች የ78 አመት ሽማግሌ በሰደፍ የደበደቡትን፣ ከአስር በላይ ወታደሮች እያዋከቡ ሰላማዊ ኢትዮጵያዊቷን ብርቱካን ሚደቅሳን በግፍ ሲያሰሩና ወደ ሶስት ወር ገዳማ በጨለማ ቤት ዉስጥ በማስቀመጥ ከፍተኛ ኢሰብአዊ ጭካኔ በማድረግ ቶርቸር የሚያደርጉትን፣ ከሁለት መቶ በላይ ኢትዮጵያዉያን በአዲስ አበባ ግንባራቸዉ ላይ ተኩሰዉ የገደሉትን፣ በኦጋዴን ከሁለት መቶ አምሳ በላይ መንደሮችን ያቃጠሉትን ... ነዉ አቶ ያዕቆብ አብርሃም ፍትህ ያስጠበቁ፣ ዲሞክራሲያዊ ሕገ መንግስት ያከበሩ እያሉ በመቀሌ ስም የጻፉት። በጣም የሚያስቅ !

ይህ የነ አቶ ያእቆብ ጥረት፣ በታሪካዊ መቀሌ ስም፣ በሕዝብ የማይደገፍን ፣ በሕዝብ ላይ ቀንበር የዘረጋንና ከጊዜ ወደ ግዜ በአለም አቀፍ መድረክ እየተገለለን የመጣን የሕወሃት መንግስት ትንሽ ገጽ በረከት ለማሰጠት የተሞኮረ ሙከራ ይመስለኛል።

ኢትዮጵያውያን በመቀሌ ስም የሚደረገዉን ንግድ ለማክሸፍ፣ አቶ ያእቆብንና መሰሎቻቸዉ ሕግና ስርዓት የሚያከብር ባሉት አገዛዝ በአደባባይ የተገደሉትን፣ የነ ሰማዕት ሽብሬ ደሳለኝን ፎቶ ይዘዉ ተቃዉሞ አቀረቡ።

በአወሮፓ ያሉ የኤምባሲ ሰራቶኞች፣ ተከፍልዋቸዉ ኢትዮጵያዉያንን እንዲሰልሉ በአዉሮፓ የሚንቀሳቀሱትና ጥቂት አገዛዙን የሚደግፉት ግለሰቦችም የራሳቸዉን ሰላማዊ ሰልፍ አደረጉ። በመቀሌ ላይ ጥቃት እንደተደረገና ሌላዉ ኢትዮጵያዊም በመቀሌ ላይ ችግር እንዳለዉ የሚያሳይ ርካሽ ፕሮፖጋንዳ በአፍቃሪ ሕወሃት ድህረ ገጾች ማሰራጨት ጀመሩ። በሌላ አባባል፣ የትግራይ ወገኖቻችን በሌላዉ ኢትዮጵያዊያን ላይ ጥያቄ ምልክት እንዲያቀርቡ፣ ሌላዉን እንዲርቁና፣ እንዲፈሩ ለማድረግ በሕወሃት ካድሬዎች የተሞከረ እኩይ ተግባር ነበር።[2] እንደዉም የመቀሌ ከንቲባ ነኝ የሚሉት የሕወሃት ካድሬ፣ አቶ ዘሪሁን ፍስሃም፣ በጉዳዩ ገብተዉበት የበለጠ ወሬዉ እንዲፋፋም የማድረግ ሙከራ እየተደረገ ነዉ።

ይህን ብዬ ወደ አንድ ሌላ በጣም ትኩረት ሊሰጠዉ የሚገባ መሰረታዊ ጉዳይ ልምጣ። በመቀሌ ሆነም በትግራይ ሕዝብ ስም ከመጀመሪያዉኑ የሕወሃት ካድሬዎች ሊነግድ እንደሚችሉ ሁላችንም የምናዉቀዉ ጉዳይ ነዉ። ነገር ግን አንዳንዶቻችን አርቆ ማስተዋል የሚጎድለን ይመስለኛል። ከአሁን ለአሁን በሕወሃት ካድሬዎች አንድ ነገር ስለተደገፈ ብቻ፣ ነገሩ ምን እንደሆነ ሳናመዛዝን ጠቃሚ ሊሆን ቢችልም በጭፍን የመቃወም ዝንባሌ አለን። ይሄ ትልቅ ስህተት ነዉ።

መቀሌ እህት ከተማ ብትሆን ልንደሰት ይገባን ነበር እንጂ በሕወሃት ካድሬዎች ስለተደገፈና መቀሌን ተጠቅመዉ ሕወሃትን የመሸጥ ሥራ ስለተሰራ፣ ልንቃወም አይገባም ነበር። ይህን በማድረጋችን ለሕወሃት ካድሬዎች መርዛቸዉን የሚረጩበት መሳሪያ ነዉ የሰጠናቸዉ። ይህን በማድረጋችን የኛም የሆነችዉን መቀሌ ለነርሱ ብቻ እንደሆነች አድርገን መቁጠራችን ነዉ የሚያሳየዉ። ወ/ት ብርቱካን ሚደቅሳ «ሜዳዉን ለኢሕአዴግ አንለቅም!» ብለዉ ነበር። ያን ሲሉ መቀሌንም ማለታቸዉ ነበር። ታዲያ እኛ መቀሌን ለምን ለእነርሱ እንለቃለን?

---

[2] http://ecadforum.com/blog/2009/03/23/no-deal-tubingen-gernamy/

**መቀሌን ማን ነዉ ለሕወሃት ብቻ የሰጠው ? መቀሌ እኮ ደማቸዉን ለኢትዮጵያ አንድነትና ነጻነት በመተማ ያፈሰሱት የጀግናዉ የአጼ ዮሐንስ ከተማ ነች ? ግብጾች ሁለት ጊዜ ኢትዮጵያን በወረሩ ጊዜ፣ አንድ ጊዜ በጉራ ሌላ ጊዜ በጉንደት ጦርነት ከፍቶ፣ በግብጾች ላይ ድል የተቀዳጀዉ በአጼ ዮሐንስ የሚመራዉ ጦር የተነሳዉ እኮ ከመቀሌ ነበር ? በቅርቡ የሕወሃትን አገዛዝ በመቃወም አረና ትግራይ ለሉዓላዊነት በጠራዉ ታላቅ ሕዝባዊ ስብሰበ ላይ የተገኘዉ በብዙ ሺህ የሚቆጠር ሕዝብ እኮ የመቀሌ ሕዝብ ነዉ ? ታዲያ መቀሌን እንደ ሕወሃት ቆጥሮ ሕወሃት ባጠፋዉ ጥፋት መቀሌ የምትቀጣበት ምክንያቱ ምንድን ነዉ ?**

ለዚህ ነዉ በቱቢንግን ከተማ የታየዉን ትልቅ ስህተት ተደርጎ መታየት ያለበት። መቀሌ የሁላችንም ከተማ ናት። መቀሌን የሚጠቅም ነገር ከማድርግ መቆጠብ የለብንም። ምንጊዜም ከመቀሌ ጎን መሰለፍ አለብን። ከሕወሃት የበለጠ እኛ ለመቀሌ አሳቢ መሆናችንን ማሳየት አለብን።

ገዢዉ ፓርቲ ከምርጫ ዘጠና ሰባት በኋላ ያደረገዉን ሁላችንም የምናስታወሰዉ ነዉ። ቅንጅት መግለጫ ያወጣል። በመግለጫዉ ኢትዮጵያዉያን የኢሕአዴግ ካድሬዎችን ፣ ነፍስ የገደሉትንና ያስገደሉት እንዲገለሉና ከነርሱም ጋር እሳት መቀባበል እንዳይኖር ጥሪ ያቀርባል። ገዢዉ ፓርቲ ይህንን መግለጫ የትግራይ ተወላጆችን ለማጥፋት እንደተደረገ አድርጎና ጠምዝዞ በማቅረብ፣ ቅንጅት የትግራይ ሕዝብ ጠላት እንደሆነ ብዙዎችን በዉሸት ለማሳመን ቻለ።

ቅንጅት በነጋታዉ «የማግለል ዘመቻዉ በወንጀለኞች ላይ እንጂ በአንድ ሕዝብ ላይ ማነጣጠር እንደሌለበት» የሚያብራራ ሌላ መግለጫ ቢያወጣም፣ ገዢዉ ፓርቲ የሚቆጣጠራቸዉ ሜድያዎች ግን ሁለተኛዉን መግለጫ አላወጡትም። ለምን ቢባል ፣ ለነርሱ ቅንጅትንና የቅንጅት ደጋፊዎችን እንደ ትግራይ ሕዝብ ጠላት አድርጎ ማቅረቡ ትልቁ መሳሪያቸዉ ስለነበረ ነዉ። በትግራይ ሕዝብና በሌላዉ ሕዝብ መካከል የጥላቻና የመፈራራት ግድግዳ ማድረጋቸዉ ለነርሱ በስልጣን መቆየት ስለሚያመቻችላቸዉ ነበር።

ካለፉት ስህተቶች መማር ያለብን ይመስለኛል። እንደገና ተመሳሳይ፣ ለገዢዉ ፓርቲ የሚመች ሁኔታ እንዲፈጠር ማድረግ የለብንም ባይ ነኝ። የትግራይ ሕዝብ የትግሉ አካል መሆን የግድ ይኖርበታል ። ሌላዉ ኢትዮጵያዊ መብቱ እንደተገፈፈዉም የትግራይ ሕዝብም መብቱ ተገፋል። ሌላዉ ኢትዮጵያዊ በባርነት ዉስጥ እንዳለም የትግራይ ሕዝብ በባርነት ላይ ነዉ ያለዉ። ሌላዉ ኢትዮጵያ የኢትዮጵያን ባንዲራ በመስቀሉ እንደሚታሰረዉ ሁሉ የትግራይ ሕዝብም ተመሳሳይ ችግር ላይ ነዉ ያለዉ።

በትግራይ የምንኖር ኢትዮጵያዉያንም ሆነ ከትግራይ ዉጭ ያለን፣ አንዳችን አንዳችንን መጥላቱንና አንዳችን አንዳችንን መፍራቱን አቁመን እንደ ኢትዮጵያዊ በጋራ አገራችንን የምናድንበት ጊዜ ነዉ። በጀርመን ቱቢግን የተፈጠረዉ አይነት ክስተት በኛ መሃከል መደገም የለበትም። ከፋፋዩ አገዛዝ ከፋፋይ ስራዉን እንዲቀጥል የሚረዳዉ መሳሪያ ማዘጋጀት የለብንም። አንገታችን የሚታረድበትን ቢላ መሳሉን አቁመን በጋራ ብንሰራ ለሁላችንም ይበጀናል። የቋውራዉ መይሳዉ ቴዎድሮስ፣ የመቀሌዉ አጼ ዮሐንስ፣ የተንቤኑ አሉላ አባ ነጋ፣ አጼ ሚኒሊክ ፣ ደጃች ባላቻ አባነፍሶ፣ ፊታዉራሪ ገበይሁ . . . ያቆዩልንን አንዲት ኢትዮጵያን በጋራ እንገንባ። በጋራ መቀሌን እንገንባ። በጋራ ቀብሪደሃርን እንገንባ። በጋራ ጊምቢን እንገንባ። በጋራ ኩታበርን እንገንባ። በጋራ ዲላን እንገንባ። በተናጥል፣ በጥላቻ በመከፋፈል፣ በመፈራራትና ባለመተማመን ሳይሆን፣ በጋራ ፣ በአንድነት፣ በፍቅር፣ ይቅር በመባባል አንድ እርምጃ ወደፊት እንራመድ !

እግዚአብሄር ልቦና ይስጠን !